Wellpoint
District of Columbia

**የ የጤና መድህን ተላላፊነት እና ተጠያቂነት አዋጅ (Health Insurance Portability and Accountability Act ,HIPAA) የግላዊነት አሰራር ማሳወቂያ**

የዚህ ማሳወቂያ የመጀመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን ኤፕሪል 14 ቀን 2003 ነበር። ይህ ማስታወቂያ በጣም በቅርብ ጊዜ ሴፕቴምበር 2025 ላይ ተሻሽሏል።

**ይህ ማስታወቂያ እርስዎን የሚመለከት የሕክምና መረጃ አገልግሎት ላይ እንዴት ሊውል እንደሚችል እና ይፋ እንደሚሆን እና ይህን መረጃ እርስዎ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይገልጻል። እባክዎ በጥንቃቄ ያንብቡት።**

ስለ ጤናዎ እና የጤና ጥቅማ ጥቅሞችዎ ያለው መረጃ ሚስጥራዊ ነው። ሕጉ ደህንነቱ የሚጠበቅ የጤና መረጃ (PHI) በመባል የሚጠራውን ይህን ዓይነት መረጃን፣ ለአባሎቻችን ደህነነቱ በጠበቀ መልኩ እንድንጠብቅ ያስገድደናል። ያ ማለት እርስዎ አሁን አባል ከሆኑ ወይም ከዚህ በፊት አባል ከነበሩ፣ የመረጃዎ ደህንነት የተጠበቀ ነው ማለት ነው።

ለጤና እቅዳችን ብቁ ሆነው ከተመዘገቡ በኋላ ለ Medicaid እና የህጻናት የጤና መድን ፕሮግራም ከስቴት ኤጀንሲዎች ስለ እርስዎ መረጃ እናገኛለን። በተጨማሪም ለጤና እንክብካቤዎ እንድንፈቅድ እና ክፍያ እንድንፈጽም፣ ከእርስዎ ሐኪሞች፣ ክሊኒኮች፣ የምርመራ ቤቶች፣ እና ሆስፒታሎች መረጃ እናገኛለን።

የፌደራል ህግ በስልክ፣ በወረቀት ጽሁፍ የተነገረንን፣ ወይም በኮምፒዩተር የተቀመጠን PHI ለመጠበቅ ማድረግ ስለሚገባን ነገሮች ለእርስዎ መንገር እንዳለብን ያስገድደናል። በተጨማሪም ደህንነቱን እንዴት እንደምንጠብቅ ልንነግርዎት ይገባል። PHI ን ለመጠበቅ፥

- በወረቀት ላይ ካለ፣ እኛ፥
  - ቢሮዎቻችንን እና ፋይሎቻችንን እንቆልፋለን
  - ሌሎች እንዳያገኙት የጤና መረጃ የያዙ መረጃዎችን እናስወግዳለን
- በኮምፒዩተር ላይ የተቀመጥ ከሆነ፣ እኛ፥
  - ትክክለኛዎቹ ሰዎች ብቻ እንዲገቡ የይለፍ ቃሎችን እንጠቀማለን
  - ሲስተሞቻችንን ለመከታተል ልዩ ፕሮግራሞችን እንጠቀማለን
- ለእኛ፣ ለሐኪሞች ወይም ለስቴት የሚሰሩ ሰዎች የሚጠቀሙት ወይም የሚያጋሩት፣ እኛ፥
  - የመረጃ ደህንነትን ለመጠበቅ መመሪያዎችን እናወጣለን (ፖሊሲዎች እና ሥነ ሥርዓቶች ተብለው ይጠራሉ)
  - ለእኛ የሚሰሩ ሰዎች መመሪያዎቹንን እንዲከተሉ እናስተምራቸዋለን

**እኛ የእርስዎን PHI መጠቀም እና ማጋራት የምንችለው መቼ ነው?**

የእርስዎ ይሁንታዎን ከነገሩን የእርስዎን PHI ለቤተሰብዎ ወይም የጤና እንክብካቤዎ ላይ እገዛ ለሚያደርግልዎ ወይም ለሚከፍልልዎት ለመረጡት ሰው ልናጋራ እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ፣ **ያለ**እርስዎ ይሁንታ ልንጠቀምበት እና ልናጋራው እንችላለን፥

- **ለህክምና እንክብካቤዎ (ህክምና)**
  - ሐኪሞች፣ ሆስፒታሎች እና ሌሎች እርስዎ የሚያስፈልግዎትን እንክብካቤ እንዲሰጡ ለመርዳት

**wellpoint.com/dc/medicaid**

1062744DCMAMWLP 09/25

DHCF Department of Health Care Finance
WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

This program is brought to you by the Government of the District of Columbia Department of Health Care Finance.

- **ለክፍያ ምክንያቶች**
  - ለእርስዎ እንክብካቤ ክፍያ ከሚጠይቁን ሐኪሞች፣ ክሊኒኮች እና ሌሎች ጋር መረጃ ለመጋራት።
  - የጤና እንክብካቤ ወይም አገልግሎቶችን ከማግኘትዎ በፊት እንደምንከፍልልዎት ከተናገርን
  - እርስዎን ለመደገፍ እና ያሉትን ጥቅማጥቅሞች እንዲያገኙ ለማገዝ
- **ለጤና እንክብካቤ ንግድ ምክንያቶች (ኦፕሬሽኖች)**
  - የኦዲት፣ ማጭበርበር እና አላግባብ መጠቀምን የመከላከል ፕሮግራሞችን፣ እቅድ ማውጣትን እና የዕለት ተዕለት ሥራን ለመርዳት
  - ፕሮግራሞቻችንን የተሻሉ ለማድረግ የሚያስችሉ መንገዶችን ለማግኘት
  - ሊረዱዎት በሚችሉ የኮምፒውተር ሥርዓቶች የታገዘ

  የእርስዎን PHI ከተለያዩ ምንጮች ልናገኝ እንችላለን፣ እና የእርስዎን PHI ለክፍያ፣ የጤና እንክብካቤ ስራዎች እና ለህክምና ለጤና መረጃ ልውውጦች ልንሰጥ እንችላለን። ይህንን የማይፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎን ለበለጠ መረጃ **wellpoint.com/privacy** ይጎብኙ።

- **ለሕዝብ ጤና ምክንያቶች**
  - የህዝብ ጤና ባለስልጣናት ሰዎችን ከመታመም ወይም ከመጎዳት እንዲጠብቁ ለመርዳት
- **ለእንክብካቤዎ እገዛ ለሚያደርጉ ወይም ለሚከፍሉ ሌሎች ሰዎች ጋር**
  - የእርስዎ ይሁንታዎን ከነገሩን፣ ለቤተሰብዎ ወይም የጤና እንክብካቤዎ ላይ እገዛ ለሚያደርግልዎት ወይም ለሚከፍልልዎት ለመረጡት ሰው ጋር
  - ስለራስዎ መናገር የማይችሉ ከሆነ እና ለእርስዎ የተሻለ ከሆነ፣ ለጤና እንክብካቤዎ እገዛ ለሚያደርግልዎት ወይም ለሚከፍልልዎት ሰው ጋር

ለሕክምናዎ፣ ክፍያ፣ የእለት ተለት ሥራ፣ የምርምር ጥናት ወይም ከታች ለተዘረዘሩት ሌሎች ነገሮች ውጪ የእርስዎን PHI ከመጠቀማችን ወይም ከማጋራታችን በፊት የእርስዎን ይሁንታ በጽሁፍ ማግኘት አለብን። ስለ እርስዎ ከሐኪምዎ የሳይኮቴራፒ ማስታወሻዎችን ከማጋራታችን በፊት የእርስዎን የጽሁፍ ይሁንታ ማግኘት አለብን። በተጨማሪም፣ የእርስዎን PHI እኛ የምንሸጥ ከሆነ ወይም ለገበያ የምንጠቀምበት ወይም የምናጋራው ከሆነ የእርስዎ የጽሁፍ ይሁንታ ያስፈልገናል።

በጽሁፍ የሰጡትን ይሁንታን መተው እንደሚፈልጉ በጽሁፍ ሊነግሩን ይችላሉ። የእርስዎ ይሁንታ ባለበት ወቅት የተጠቀምነውን ወይም ያጋራነውን መመለስ አንችልም። ነገር ግን ወደፊት የእርስዎን PHI መጠቀም ወይም ማጋራት እናቆማለን።

**ሌሎች መንገዶች - ወይም ህጉ የሚፈቅድልን - የእርስዎን PHI እንድንጠቀም፥**

- ፖሊስን እና ሌሎች ህግ የሚያስከብሩ ሰዎችን ለመርዳት
- በደል እና ቸልተኝነት ሪፖርት ለማድረግ
- እንደ የፍርድ ቤት ትዕዛዞች ላሉ ህጋዊ ሰነዶች ምላሽ ለመስጠት
- እንደ ኦዲት ወይም ምርመራዎች ላሉ ዓላማ ለጤና ቁጥጥር ኤጀንሲዎች መረጃ ለመስጠት
- የእርስዎን ስም እና የሞት መንስኤ ለማወቅ እንዲረዳቸው ለሬሳ ምርመራ ሐኪሞች፣ የህክምና መርማሪዎች ወይም የቀብር አስፈጻሚዎች።
- የሰውነት ክፍሎችዎን ለሳይንስ
- ወይም ለጥናት ምርምር ለመስጠት ሲጠይቁ ለመርዳት
- እርስዎን ወይም ሌሎች ከመታመም ወይም ከፉኛ ከመጎዳት ለመጠበቅ።
- ለመንግስት የሚሰሩ ሰዎችን እንደ በጥቅማጥቅሞች ላይ አርበኞችን እንደ መርዳት ባሉ አንዳንድ ስራዎች መርዳት
- በሥራ ቦታ ከታመሙ ወይም ከተጎዱ ለሠራተኞች ካሳ መረጃ ለመስጠት
- ለጤና እና ለሰብአዊ አገልግሎት ሚኒስትር የ HIPAA ደንቦችን በተግባር ላይ ለማዋል የሚረዱ መረጃዎችን ለመስጠት።

**መብቶችዎ ምንድን ናቸው?**

- የእርስዎን PHI ለማየት እና ቅጂውን ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ። ወደ እርስዎ ለመላክ 30 ቀናት ይኖረናል። ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለገን፣ ለእርስዎ ማሳወቅ አለብን። ነገር ግን ሙሉ የሕክምና መረጃዎ የለንም። **ሙሉ የህክምና መረጃዎን ቅጂ ከፈለጉ፣ ሐኪምዎን ወይም የጤና ክሊኒክዎን ይጠይቁ።**
- የሆነ ችግር አለ ወይም የጎደለ ነገር አለ ብለው ካሰቡ ያለንን የእርስዎን የሕክምና መረጃ እንድንቀይረው እኛን መጠየቅ ይችላሉ። ወደ እርስዎ ለመላክ 60 ቀናት ይኖረናል። ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለገን፣ ለእርስዎ ማሳወቅ አለብን።
- አንዳንድ ጊዜ፣ የእርስዎን PHI እንዳናጋራ ሊጠይቁን ይችላሉ። ነገር ግን በጥያቄዎ የግድ መስማማት የለብንም ።
- ካለን የእርስዎ አድራሻ ውጪ ወዳለ አድራሻ ወይም በተወሰነ ሌላ መንገድ PHI እንድንልክልዎ እኛን መጠየቅ ይችላሉ። ባለን የእርስዎ አድራሻ መላክ እርስዎን አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ ይህን ማድረግ እንችላለን።
- ባለፉት ስድስት ዓመታት የእርስዎን PHI ለሌላ ሰው ያጋራንበትን ሁሉንም መረጃ እንድንነግርዎ ሊጠይቁን ይችላሉ። ይህ ለጤና እንክብካቤ፣ ለክፍያ፣ ለዕለትተዕለት የጤና እንክብካቤ ሥራ ወይም እዚህ ባልዘረዘርናቸው ሌሎች ምክንያቶች ያጋራንበትን ጊዜ አያካትትም። ወደ እርስዎ ለመላክ 60 ቀናት ይኖረናል። ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለገን፣ ለእርስዎ ማሳወቅ አለብን።
- የዚህን ማስታወቂያ ቅጂ በኢሜይል እንዲላክልዎ የጠየቁ ቢሆንም እንኳን የወረቀት ቅጂ እንዲላክልዎ በማንኛውም ጊዜ መጠየቅ ይችላሉ።
- ለአንድ አገልግሎት ሙሉዉን ክፍያ ከከፈሉ፣ ስለዚያ አገልግሎት መረጃውን ለእኛ እንዳያጋሩ ሐኪምዎን መጠየቅ ይችላሉ።

**እኛ ምን ማድረግ አለብን?**

- ህጉ በዚህ ማስታወቂያ ከገለጽነው ውጪ የእርስዎን PHI ሚስጥራዊ ማድረግ እንዳለብን ያስገድዳል።
- ህጉ ስለ ሚስጥራዊነት እንድናደርግ የሚያስገድደን ምን እንደሆነ ለእርስዎ መንገር አለብን።
- በዚህ ማስታወቂያ እናደርጋለን ብለን የገለጽናቸውን ነገሮች ማድረግ አለብን።
- ለምሳሌ አደጋ ውስጥ መሆንዎንይየሚገልጹ ትርጉም ያላቸው ምንክኒያቶች ጠቅሰው ከጠይቁንየእርስዎን PHI ወደ ሌላ የሆነ አድራሻ፣ ወይም መደበኛ ከሆነው ፖስታ ውጪ በሌላ መንገድ የመላክ ግዴታ አለብን።
- መረጃዎን እንዳናጋራው ከነገሩን በኋላ የእርስዎን PHI ማጋራት ካለብን ለእርስዎ መንገር አለብን።
- እኛ እዚህ እናደርጋቸዋለን ብለን ከገለጽናቸው በላይ የስቴት ህጎች ማድረግ እንዳለብን የሚያስገድዱ ከሆነ፣ እነዚህን ህጎች እንከተላለን።
- የእርስዎ PHI እንደተጣሰ ካሰብን እኛ ለእርስዎ ማሳወቅ አለብን።

**ሌሎች ሕጎች**

HIPAA የእርስዎን የግል የጤና መረጃ ለመጠበቅ የሚረዳ የግላዊነት ደንብ ነው። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ለግላዊነትዎ የበለጠ ጥበቃ የሚሰጡ ሌሎች ደንቦች አሉ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ HIPAA ን ብቻ ሳይሆን እነዚያንም ደንቦች መከተል ይኖርብናል።

ለምሳሌ፣ ከአደንዛዥ ዕፅ ወይም ከአልኮል ጋር በተያያዙ የሱሰኝነት ችግሮች (SUD) መረጃዎች ላይ ልዩ ጥንቃቄ የሚያደርጉ ሕጎች አሉ። ከእንደዚህ? ዓይነት መረጃዎች ጋር ስንሠራ፣ በጣም ጥንቁቅ መሆን እና ልዩ ደንቦቹን መከተል አለብን። የ SUD መረጃዎችን ለሕክምና፣ ለክፍያ እና ለጤና አገልግሎት አ?ስተዳደር ተግባራት ልንጠቀምባቸው እና ልናጋራቸ?ው እንችላለን።

በአንዳንድ ሁኔታዎች ይህ መረጃ እንዴት እንደሚጋራ "እሺ" ወይም "አይ" የማለት መብት አለዎት። ሐሳብዎን ከቀየሩ፣ በማንኛውም ጊዜ በጽሁፍ በማሳወቅ የሰጡትን ፈቃድ መሰረዝ ይችላሉ።

**እርስዎን ማነጋገር**

እኛ፣ ከተባባሪዎቻችን እና/ወይም አቅራቢዎቻችን ጋር፣ አውቶማቲክ የስልክ መደወያ ስርዓት እና/ወይም ሰው ሰራሽ ድምጽ በመጠቀም መደወል ወይም የጽሁፍ መልዕክት ልንልክልዎት እንችላለን። ይህንን የምናደርገው በስልክ የደንበኞች ጥበቃ ህግ (TCPA) መሰረት ብቻ ነው። የስልክ ጥሪዎቹ ስለ ሕክምና አማራጮች፣ ወይም ሌሎች ከጤና ጋር የተያያዙ ጥቅማጥቅሞችን እና አገልግሎቶችን ለማሳወቅ ሊሆኑ ይችላሉ። በስልክ እንድናገኝዎት ካልፈለጉ፣ ስልኩን ለደወለው ሰው ያሳውቁ፣ እና ከአሁን በኋላ በዚህ መንገድ አናገኝዎትም። ወይም የእርስዎን ስልክ ቁጥር "አይደወል" በሚለው ዝርዝራችን ውስጥ ለማስገባት በ **844-203-3796 (TTY 711)** መደወል ይችላሉ።

**ጥያቄዎች ካሉዎትስ?**
ስለ የኛ የሚስጥራዊነት መመሪያችን ጥያቄዎች ካልዎት ወይም መብቶችዎን መጠቀም ከፈለጉ፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ **833-359-1384** ይደውሉ። መስማት የተሳነዎ ከሆኑ ወይም የመስማት ችግር ካለብዎት፣ በ **TTY 711** ይደውሉ።

**የበለጠ መረጃን ለማየት**
የእርስዎን መረጃ እንዴት እንደምንሰበስብ እና እንደምንጠቀምበት፣ ስለ ግላዊነት መብቶችዎ፣ እንዲሁም ስለ ሌሎች የክልል እና የፌዴራል የግላዊነት ሕጎች ተጨማሪ መረጃ ለማንበብ እባክዎን የድረ-ገጻችንን የግላዊነት ገጽ በ **wellpoint.com/privacy** ይጎብኙ ወይም ለተመዝጋቢዎች አገልግሎት ክፍል በ ይደውሉ **833-359-1384 (TTY 711)**.

**ቅሬታ ካለዎትስ?**
እኛ እዚህ ያለነው ለማገዝ ነው። የእርስዎ PHI ደህንነቱ እንዳልተጠበቀ ከተሰማዎ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ወይም የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንትን ማግኘት ይችላሉ። ቅሬታ ስላሰሙ፣ ምንም መጥፎ ነገር አይደርስብዎትም።

**ለጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቾች መምሪያ ይጻፉ ወይም ይደውሉ፥**
Office for Civil Rights
U.S. Department of Health and Human Services
200 Independence Ave SW,
Washington, DC 20201

ይህን የጤና መድን ተንቀሳቃሽነት እና ተጠያቂነት ህግ (HIPAA) ማስታወቂያ እና የእርስዎን PHI ደህንነት የምንጠብቅባቸውን መንገዶች የመቀየር መብታችን የተጠበቀ ነው። እንዲያ ከሆነ፣ እኛ ስለለውጦቹ በመጽሄቶች እንነግርዎታለን። በተጨማሪም በድህረ-ገጽ በ **wellpoint.com/dc/medicaid** ላይ እንለጥፋቸዋለን።

**ዘር፣ ብሔር፣ ቋንቋ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ የጾታ ማንነት እና ከጤናዎ ጋር የተያያዙ ሌሎች ማህበራዊ ሁኔታዎች**
ስለ እርስዎ ዘር፣ ብሔር፣ ቋንቋ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ የጾታ ማንነት እና ከጤናዎ ጋር የተያያዙ ሌሎች ማህበራዊ ሁኔታዎችን (እንደ መኖሪያ ቤት፣ ትራንስፖርት ወይም ጤናማ ምግብ ያሉ) መረጃዎችን ልንሰበስብ፣ ልንገምት፣ ልንቀበል እና/ወይም ልንይዝ እንችላለን። ይህን መረጃ በዚህ ማስታወቂያ ላይ እንደተገለጸው እንጠብቀዋለን።

ይህንን መረጃ ለሚከተሉት እንጠቀማለን፥
- የሚያስፈልግዎትን መረጃ ማግኘትዎን ለማረጋገጥ
- የጤና ውጤቶችን የሚያሻሽሉ ፕሮግራሞችን ለመፍጠር
- የጤና ትምህርት መረጃን ለማዘጋጀት እና ለመላክ
- ስለ ቋንቋ ፍላጎቶችዎ ለሐኪሞች ለማሳወቅ
- የቃል ትርጉም እና የትርጉም አገልግሎቶችን ለመስጠት

ይህንን መረጃ ለሚከተሉት <u>**አንጠቀምበትም**</u>፥
- የጤና መድን ለመስጠት
- ለአገልግሎቶች ምን ያክል ለማስከፈል ለመወሰን
- ጥቅማጥቅሞችን ለመወሰን
- ላልጸደቁ ተጠቃሚዎች ለማጋራት

***የግል መረጃዎ***

በዚህ ማስታወቂያ ላይ እንደተናገርነው የግል መረጃን (PI) ልንጠይቅ፣ ልንጠቀም እና ልናጋራ እንችላለን። የእርስዎ PI ለህዝብ ይፋ አይደለም እና እርስዎ ማን እንደሆኑ ይነግረናል። አብዛኛውን ጊዜ የሚወሰደው ለመድን ዓላማ ነው። PI እንደ እርስዎ የሚጠቀሙባቸው የድር ጣቢያ የተጠቃሚ ስሞች እና የይለፍ ቃሎች፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥሮች፣ እና የስራ ታሪክዎ ያሉ የተለያዩ ነገሮችን ሊያካትት ይችላል። የእርስዎ PI ከእርስዎ የጤና እንክብካቤ ወይም የጤና እቅድዎ ጋር የሚገናኝ ከሆነ ከ PHI ጋር አንድ አይነት ሊሆን ይችላል። በዚህ ማስታወቂያ ላይ እንደተነጋገርነው የእርስዎን PI እና የእርስዎን PHI እንደህንነት ጠብቃለን።

- የእርስዎን PI ስለእርስዎ የሚከተሉትን ውሳኔዎች ለመወሰን ልንጠቀም እንችላለን፡-
  - ጤና
  - ልማዶች
  - የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያዎች
- ስለ እርስዎ PI ከሌሎች ሰዎች ወይም ቡድኖች ልናገኝ እንችላለን ለምሳሌ፡-
  - ሐኪሞች
  - ሆስፒታሎች
  - ሌሎች የመድን ኩባንያዎች
- በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ፣ የእርስዎን ይሁንታ ሳናገኝ፣ ከኩባንያችን ውጪ ላሉ ሰዎች ወይም ቡድኖች PI ልናጋራ እንችላለን።
- ማንኛውንም ነገር ከማድረጋችን በፊት የመከልከል እድል ለእርስዎ ለመስጠት እናሳውቅዎታለን።
- የእርስዎን PI እንድንጠቀም ወይም እንድናጋራ ካልፈለጉ ለኛ እንዴት እንደሚያሳውቁን እንነግርዎታለን።
- የእርስዎን PI የማየት እና የመቀየር መብት አሎት።
- የእርስዎ PI ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን እናረጋግጣለን።

ይህ መረጃ በሌሎች ቋንቋዎች በነጻ ይገኛል። እባክዎን በተመዝጋቢዎች አገልግሎት ቁጥራችን **833-359-1384 (TTY 711)** ከ?ሰኞ እስከ አርብ ከ 8:00 a.m.(ጠዋት) እስከ 6:00 p.m. (ከሰዓት) ባለው ሰዓት ውስጥ ይደውሉልን።

በ Wellpoint District of Columbia, Inc. የሚሰጥ ሽፋን

የተሻሻለው ሴፕተምበር፣ 2025